# [የኢትዮጵያውያን ዓመታዊ የስፖርት (የፍን) ፤ የባሕል ዝግጅትና መታረም የሚገባቸው ስሕተቶች ከሕዝባዊው ትግል አንጻር! – ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው]

**July 20, 2017**

ዘንድሮ ሲያትል ላይ በተደረገው 34ኛው ዓመታዊ የስፖርት (የፍን, ፍን ሲነበብ ን ትጠብቃለች) እና የባሕል በዓል ወይም ዝግጅት በተለይ ሁለት የጎሉና በፍጹም መደገም የሌለባቸው ችግሮች ተከስተዋል፡፡



1ኛው. የፀረ ኢትዮጵያው የጥፋት ኃይል የወያኔ አገልጋይ በመሆናቸው ሕዝብ ለጠላቸውና ያስቀየሙትን የበደሉትን ያደሙትንም ሕዝብ ይቅርታ ላልጠየቁ ከያኔያን ከሕዝቡ ፍላጎት ውጪ አስቀድሞ ሕዝቡ እንዲያውቀው ባልተደረገበት ሁኔታ ዕድል መስጠቱ፡፡

2ኛ. የፀረ ኢትዮጵያ የጥፋት ኃይሎች የወያኔና የኦነግ ደጋፊዎችና የቤተሰብ አባላት ማንነታቸውን በግልጽ በሚያሳይ መልኩ በቦታው መገኘታቸው፡፡ የሚሉት ናቸው፡፡

ይሄንን ዓመታዊ ዝግጅት በየዓመቱ ያዘጋጁ ዘንድ በሕዝብ ኃላፊነት የተሰጣቸው አዘጋጆቹ ከሕዝቡ ፍላጎት ውጭ ወይም በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምነውንና ኢትዮጵያዊነቱን የሚጠብቀውን ሕዝብ የሚያስቆጣ አሚያስከፋ አንዳችም ነገር ማድረግ ፈጽሞ እንደሌለባቸውና የግድ የሕዝቡን ፍላጎት ማክበር እንደሚኖርባቸው ጠንቅቀው የሚያውቁ አልመሰለኝም፡፡ በመሆኑም ነው በየግል ግብታዊ ውሳኔዎች ስሕተቶች እየተፈጸሙ ያሉት፡፡

ለምሳሌ፡- ሐመልማል አባተ እንደምትቀርብና ስትቀርብም በምን አግባብ እንደምትቀርብ አስቀድሞ ምንም የተገለጸ ነገር አልነበረም፡፡ ባለመኖሩም እዛው ላይ ለጥፋቷ ይቅርታ ጠይቃ ዝግጅቷን

ያቀረበች ቢሆንም ይህ ጉዳይ ሕዝቡን አስቀይሟል አስከፍቷል አስቆጥቷል፡፡ መከፋቱም ተገቢና የሚጠበቅም ነው፡፡ አስገራሚው ነገር ደግሞ ጎሳየ ተስፋዬ በተለያየ መንገድ ሕዝብ በዳሸን ቢራ ደጋፊነት (ስፖንሰርነት) በተዘጋጀው የግዮኑ ዝግጅት ላይ እንዳይጫወት “ተው!” እያለው ከወያኔ የንግድ ድርጅት ጋር በመሥራቱ ምክንያትና ሳያውቅ ሠርቶ ከሆነም ይቅርታ መጠየቅ ሲኖርበት ይቅርታ ለመጠየቅም ፈቃደኛ ሆኖ ባለመገኘቱ በዚህ ዓመታዊ የስፖርት (የፍን) እና የባሕል ዝግጅት ላይ እንዳይቀርብ የተደረገ ሆኖ እያለ በተደጋጋሚ የወያኔ መጠቀሚያና አገልጋይ የሆነችው ሐመልማል አባተ መቅረቧ ነው፡፡

ይህ ስሕተት ሕዝብን ከመናቅ የተፈጸመ ስሕተት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም፡፡ ተጠሪነቱ ለሕዝብ የሆነውና ተሳስቶ ሲገኝ ኃላፊነቱን በሰጠው በሕዝቡ ሥልጣኑን ሊነጠቅ የሚችለው አዘጋጁ ክፍል በምን አግባብ ይሄንን ሊያደርግ እንደቻለና ስሕተቱ እንዴት ሊፈጠር እንደቻለ በሚገባ ግልጽ ሳያደርግ ወደ ቀጣይ ሥራ መሸጋገር አይኖርበትምና ይሄንን ጉዳይ ግልጽ ያድርግ፡፡ የዚህ ዓመታዊ ሕዝባዊ በዓል ወይም ዝግጅት ባለቤት ኢትዮጵያዊነቱን መጠበቅና መንከባከብ የሚፈልገው፣ በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደረው ሰሜን አሜሪካ ኗሪ የሆነው የኢትዮጵያዊው ማኅበረሰብ ነው እንጅ እነ እከሌ እነ እከሌ የሚባሉ ግለሰቦች አይደለም፡፡ በመሆኑም መሥራች አባልም ይሁን ማን የሕዝብ አመኔታን ካጣና ክህደት ከፈጸመ ሕዝቡ ሊሽረውና በሚታመን ሰው ሊተካው ይችላል፡፡ ይሄንን ጉዳይ አገለግላለሁ ብሎ የገባው ሁሉ ጠንቅቆ ሊያውቅ ይገባል፡፡ ይሄንን ማወቃቸው ከመሳሳትና በማን አለብኝነትና ሕዝብን በመናቅ አግባብ ያልሆነን ተግባር ከመፈጸም እንዲቆጠቡ ያደርጋል፡፡

የሐመልማል አባተ ሳትጠበቅና ሳይነገር በድንገት መቅረብ ሸፍጥ እንዳለበት የሚያመላክተው ሌላው ጉዳይ ደግሞ የተናገረችው ቃል ነው፡፡ ሐመልማል የተናገረችው ቃል “እኛ አርቲስቶች በሆነ ምክንያት ከወያኔ ጋር በመሥራት ብናስቀይማቹህ ሁሌም ቢሆን ይቅርታ ለማድረግ ዝግጁ ሁኑ!” የሚል እንድምታ ያለው አነጋገር ነው የተናገረችው፡፡ ይሄ ደግሞ ከወያኔ ጋር ላለመሥራት፣ ሀገርንና ሕዝብን ላለመጉዳትና ላለማስከፋት፣ የወያኔ መጠቀሚያ ላለመሆንና ላለመርከስ በመቁረጣቸው በወያኔ የተለያየ በደልና ግፍ እየተፈጸመባቸው ስንት መሥዋዕትነት የከፈሉና እየከፈሉ ያሉ ከያኔያንን ተጋድሎ ዋጋና ክብር የሚያሳጣ ከመሆኑም በተጨማሪ ወደፊትም ወያኔን በማገልገላቸው ለሚፈጽሙት ጥፋት ማንም ሳይናገራቸው ወያኔን ሳይሳቀቁ እንደፈለጉ ማገልገል የሚችሉበትን ነጻነት ለመፍጠር ለማግኘት የታሰበ ሸፍጥ የታጀለበት አነጋገር ነው የተናገረችው፡፡ በመሆኑም ይህ ጉዳይ እንደቀላል ታይቶ መታለፍ እንደሌለበት በሰሜን አሜሪካ ለሚኖረው ወገን አጥብቄ ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የተያያዘው ሕዝባዊ ትግል ያልገባቸው አንዳንድ ግለሰቦች ሕዝቡ ከያኔያን (አርቲስቶች) ወያኔን እንዳያገለግሉ፣ የወያኔ መጠቀሚያ እንዳይሆኑ ያለውን የጸና አቋም ትክክል ያለመሆን ለማስረዳት የሚናገሯቸው የደነቆሩ አነጋገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌም “መሐንዲሱ አይ አንተ የወያኔ ባለሥልጣን ነህና ለአንተ ቤት ወይም ሕንፃ ንድፍ አላወጣም! እንደማይለው ሁሉ፣ ሐኪሙ አይ አንተ የወያኔ ባለሥልጣን ነህና አንተን አላክምም! እንደማይለው ሁሉ ከያኔያንም በዚሁ መልኩ መታየት አለባቸው! ልጆች ያሏቸው አሉ ባገኙት ቦታ ሠርተው ልጆቻቸውን ማሳደግ ይኖርባቸዋል!” ይላሉ፡፡ ነገር ግን ሲጀመር ማን ነው ወያኔን ማገልገል የሌለባቸው ከያኔያን ብቻ ናቸው ያለው? በሕዝባዊ ትግል ውስጥ ሁሉም ዜጋ ተዋንያን ወይም ተሳታፊ ነው እንጅ ከያኔያንና ታጋዮች ብቻ አይደሉም ተዋንያኖች ወይም ተሳታፊዎች፡፡ መሐንዲሱ “አንተ የወያኔ ባለሥልጣን ነህና ለአንተማ አልሠራም!” ማለት ካልቻለ፣ ሐኪሙም የወያኔ ባለሥልጣን ታካሚ ሲያጋጥመው መርዞ እስከመግደል ድረስ ቁርጠኛ ካልሆነማ ታዲያ ምኑን ሕዝባዊ ትግል ሆነ? በዚህ ሁኔታማ ትግሉ የጥቂቶች ትግል ይሆናል እንጅ እንዴት ሆኖ ሕዝባዊ ትግል ሊባል ይችላል? እንዴትስ ውጤታማ ሊሆን ይችላል?

“ሐኪሙ ሐኪም ስለሆነ እንዲህ ዓይነት ጥቃት በታካሚው ላይ ለመፈጸም ሞያዊ ሥነምግባሩ አይፈቅድለትም!” ልትለኝ ነው? የወያኔ ሐኪሞች ወገናችን ባላወቀው መንገድ አምካኝ መርፌ እየወጉ ሲያመክኑ፣ የትራኮማ መከላከያ እያሉ እየወጉ ወገናችንን በገዳይ መርፌ ሲፈጁ፣ በኤች. አይ. ቪ. ቫይረስ (ተህዋስ) ሲበክሉ ወዘተረፈ. የሞያ ሥነምግባሩ ፈቅዶላቸው ነው ይሄንን ያደረጉት? የአሜሪካ የሕክምና ባለሞያዎች የሩሲያንና ጠላት የሚሏቸውን ሀገራት ባለሥልጣናት፣ የሩሲያዎችም የአሜሪካኖችን እየመረዙ የሚያጠፉት የሕክምና ሥነምግባሩ ፈቅዶላቸው ይመስላቹሀል? አይምሰላቹህ! የትግል አንዱ ስልት ስለሆነ ነው፡፡

ቆይ! ቆይ! “ልጆቻቸውን ያሳድጉበት!” ምንትስ የሚባለው ልጆች ያሏቸው ከያኔያን ብቻ ናቸው እንዴ? ጋዜጠኞችስ፣ ፖለቲከኞችስ (እምነተ አሥተዳደራውያንስ) ፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችስ፣ ተበዳይ ተገፊ ዜጎችስ ወዘተረፈ. ልጆች የሏቸውም ወይ? ነው ወይስ የእነሱ ልጆች ከሰው አይቆጠሩም፣ የሰውነት ክብር የላቸውም እያላቹህን ነው? ትግሉን ሁሉም ዜጋ የራሱ ካላደረገውና በቁርጠኝነት ካልታገለማ በጥቂት ወገኖች መሥዋዕትነት ብቻ ምንም ሊመጣ የሚችል ነጻነትም ሆነ ድል አይኖርም፡፡ ሕዝባዊ ትግል ማለት እከሌ ከእከሌ ሳይባል በተለያየ የትግል ስልት ሁሉም ተሳታፊ የሚሆንበት ትግል ማለት ነው፡፡ ወያኔ በሀገርና በሕዝብ ላይ በሚፈጽመው በደልና ግፍ ተጎጅ የማይሆን ዜጋ ሊኖር ስለማይችል፣ ወያኔ ተወግዶም ዲሞክራሲያዊ (መስፍነ ሕዝባዊ) ሥርዓት መመሥረት ቢቻል ተጠቃሚ የማይሆን ዜጋ ሊኖር ስለማይችል የኢትዮጵያ ሕዝብ እያደረገው ባለው ሕዝባዊ ትግል ማንም ራሱን ገለልተኛ ሊያደርግ አይችልም፡፡ በዚህ ሕዝባዊ ትግል ተሳታፊ ለመሆን የሁሉም ኢትዮጵያዊ የዜግነት ግዴታ ነው፡፡ በትግሉ ከባባድ ዋጋና መሥዋዕትነት መክፈሉ የማይቀር ነገር ነው፡፡ ዋጋና መሥዋዕትነት ሳይከፈል ድልና ነጻነት ሊገኝ እንደማይችል ተገንዝበን ሁላችንም በቆራጥነት መሰለፍ ይኖርብናል፡፡ ሕዝብ በዚህ ደረጃ ካበረና ከተባበረ የመከራው ጊዜ አጭር ስለሚሆን የምንከፍለው ዋጋና መሥዋዕትነት ሊያሳስበን አይገባም፡፡ ማበርና መተባበር ያልቻልን እንደሆነና ትግሉን ለጥቂቶች ብቻ የተውነው እንደሆነ ነው የመከራ ዘመናችን የሚራዘመውና ማለቂያ አልባ የሚሆነው፡፡

ወደሁለተኛው ነጥብ ሳልፍ፡- በዘንድሮው ዝግጅት የወያኔ ባለሥልጣናት ልጆችና የወያኔና የኦነግ ደጋፊዎች አርማዎቻቸው የታተሙባቸውን አልባሳት በመልበስ መታደማቸው ተስተውሏል፡፡ አዘጋጁ ክፍል በምን ምክንያት እነኝህን ግለሰቦች እንዳስተናገደ ሊገባኝ አልቻለም፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ ከያኔ ፋሲል ደሞዝ አትገባም ተብሎ በተከለከለበት ሁኔታ እነኝህ ግለሰቦች የሚደግፏቸውን የወያኔና የኦነግ ፀረ ኢትዮጵያ የጥፋት ኃይሎች አርማዎች የታተሙባቸውን አልባሳት ለብሰው እንዲገኙ እንዴት ሊፈቀድላቸው እንደቻለና ፋሲል ደሞዝም ለምንና እንዴት ሊከለከል እንደቻለ ፈጽሞ ሊገባኝ አልቻለም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አዘጋጁ ክፍል ማብራሪያ መስጠት ካልቻለ የሆነ የተደበቀ ሸፍጥ መኖሩን ያመለክታልና ከባድ ችግር የሚፈጠር ይሆናል፡፡ እነኝህ የፀረ ኢትዮጵያ የጥፋት ኃይሎች የወያኔና የኦነግ ደጋፊዎች የተገኙት ብጥብጥና ረብሻ ለማስነሣት በማሰብ እንደነበረ የተገኙት ለመገመት ጠንቋይ መሆን አይጠይቅም፡፡ በግልጽ መረዳት እንደሚቻለው አርማቸው ያለበትን ልብስ ለብሰው የመገኘታቸው ዓላማ ይሄው ነው፡፡

ይሄ በሆነበት ሁኔታ ይህ ዓመታዊ ዝግጅት ፀረ ኢትዮጵያ አቋምና አስተሳሰብ ያለቸውን ግለሰቦችንና ቡድኖችን የማያካትት የማይመለከት፣ ኢትዮጵያዊነቱን መጠበቅና መንከባከብ የሚፈልገው ኢትዮጵያዊ ማኅበረሰብ በዓል ወይም ዝግጅት ሆኖ እያለ አዘጋጁ ክፍል እነኝህን ፀረ ኢትዮጵያ አቋም የሚያቀነቅኑ የፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ደጋፊ ግለሰቦችን በዓሉ ፈጽሞ የማይመለከታቸው በመሆኑ በፀጥታ ኃይል ከአካባቢው እንዲርቁ ማድረግ ሲገባው እንዴት ሊያስተናግዳቸው እንደቻለ ምንም ሊገባኝ አልቻለም፡፡ ወይ ደግሞ አዘጋጅ ክፍሉ ምን ማድረግ እንዳለበት፣ በምን ጉዳይ ላይ ምን ዓይነት አቋምና መርሕ መያዝ እንዳለበት የማያውቅ፣ ነገሮችን እንደመሰለው በግምት የሚሠራ ሆኖ እንደሆነም ችግሩ ሊፈጠር የቻለው አላውቅም፡፡

ዘንድሮን በሕዝቡ ትዕግሥት ከፀረ ኢትዮጵያ የጥፋት ኃይሉ ጭፍራ ጋር ግጭት ሳይፈጠር ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡ ከርሞ ግን በእርግጠኝነት እነኝህ የፀረ ኢትዮጵያ ጭፍሮች "መለያ ልብሳችንን ለብሰን በመገኘታችን ብቻ ብጥብጥ በማስነሣት ዝግጅቱን ማወክ እንችላለን!" ብለው የተገኙት ግለሰቦች በዚህ ድርጊታቸው በሕዝቡ ትዕግሥት ብጥብጥ እንዳልተነሣ ዓይተዋልና ከርሞ ግን ከዚህ የከፋ ተንኳሽ ተግባራትን ለመፈጸም ተዘጋጅተው የሚገኙ ይሆናል፡፡

የዘንድሮው ድርጊታቸው ድንገተኛ በመሆኑ ዘንድሮን ታግሶ ያሳለፈው ሕዝቡ ግን እንኳንና ሌላ ተንኳሽ ተግባራት ተጨምሮበት ዘንድሮ ያደረጉትን ድርጊት ብቻ እንኳ በሚቀጥለው ዓመት የሚያደርጉ ቢሆን ሕዝቡ ከዘንድሮው ዝግጅት በኋላ በተለያዩ መንገዶች ተነጋግሮ አቋም የያዘበት ሁኔታ ስለሆነ ያለው ከባድ ችግር ሊፈጠር እንደሚችል ከወዲሁ ታውቆ አዘጋጅ ክፍሉ የፀረ ኢትዮጵያ ኃይል ደጋፊዎች በፀረ ኢትዮጵያ አቋም አቀንቃኝነታቸው ይህ የኢትዮጵያና የሕዝቧ ክብር፣ ልዕልና፣ አንድነት፣ ታሪክ፣ ህልውና፣ ባሕል፣ እሴቶች የሚዘከርበት የሚከበርበት የሚወደስበት በዓል ወይም ዝግጅት የጥፋት ዓላማና ድርጊታቸውን ጥለው እስካልቀረቡ ጊዜ ድረስ በዓሉ ወይም ዝግጅቱ ፈጽሞ የማይመለከታቸው በመሆኑ መገኘት እንደማይችሉ ቢገኙ ግን በጸጥታ ኃይል ከበዓሉ እንዲገለሉ የሚደረጉ መሆኑን በማስታወቅ መውሰድ ያለበትን የእርምት እርምጃ ይወስድ ዘንድ አዘጋጅ ክፍሉን አስቀድሜ ማስጠንቀቅ እወዳለሁ፡፡ እኛ የምናከብረው እነሱ እያጠፉት ያለውን እሴታችንን በመሆኑ ሁለት ተፃራሪ አቋምና ዓለማ ይዘን ፈጽሞ በአንድ ልንታደም አንችልም አይገባንምምና፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!
ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com